ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ　　ጁማዳአል ኡላ 20/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚንስቴር　ዲሴምበር 24/2021 ግ.

# በቅዱስ ቁርኣን የሙእሚኖች ባሕርይ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ لَهُمْ جَنَّاتٌ تَجْرِي مِن تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ ذَٰلِكَ الْفَوْزُ الْكَبِيرُ}**

ለአለው ለአማቱ ጌታ ይገባው የአንቀጹዋ ትርጉም፡

(እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችንም የሠሩ ለእነርሱ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች አሏቸው፡፡ ይህ ታላቅ ማግኘት ነው፡፡)

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስከራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቄያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዘህም በምቀጠል
እምነት አላህ ለሰው ልጅ ከለገሳቸው ተድላዎች በጣም ታላቁ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{بَلِ اللَّهُ يَمُنُّ عَلَيْكُمْ أَنْ هَدَاكُمْ لِلْإِيمَانِ إِنْ كُنْتُمْ صَادِقِينَ}**

(ይልቁንም አላህ ወደ እምነት ስለ መራችሁ ይመጻደቅባችኋል፤ እውነተኞች ብትኾኑ» (መመጻደቅ ለአላህ ነው) በላቸው፡፡)

እምነት በጸጥታ ለተሞላና ለተረጋጋ ህይወት፣ ለስኬትና ከአላህ ዘንድ ለሚገኝ ታላቅ ምንዳ ቀጥተኛው መስመር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{مَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَى وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ}**

(ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፡፡ ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን፡፡) አንድህም ይላል፡

**{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُواْ وَعَمِلُواْ الصَّالِحَاتِ وَأَقَامُواْ الصَّلاَةَ وَآتَوُاْ الزَّكَاةَ لَهُمْ أَجْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ وَلاَ خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلاَ هُمْ يَحْزَنُونَ}.**

(እነዚያ ያመኑ፡፡ መልካም ሥራዎችንም የሠሩ፡፡ ሶላትንም ያስተካከሉ፡፡ ዘካንም የሰጡ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው፡፡ በእነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም እነርሱም አያዝኑም፡፡)

የተከበረውን ቁርኣን ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው አላህ (ሰ.ወ.) ባሮቹን በቅዱስ ቁርኣን በተለያዩ ባህርዮች ያሞገሳቸው መሆኑን በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፡ ከነሱም በቅድሚያ የሚጠቀሰው፡ ሰግደትን ጊዜውን ጠብቆ፣ ማእዘናቱን አሟልቶና ልቡን አሰባስቦ መስገድ የሚለው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{قَدْ أَفْلَحَ الْمُؤْمِنُونَ * الَّذِينَ هُمْ فِي صَلَاتِهِمْ خَاشِعُونَ}**

(ምእምናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ)፡፡እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ውስጥ (አላህን) ፈሪዎች፡፡) አንድህም ይላል፡

**{ وَالَّذِينَ هُمْ عَلَى صَلَوَاتِهِمْ يُحَافِظُونَ}.**

(እነዚያም እነሱ በስግደቶቻቸው ላይ የሚጠባበቁ የኾኑት (አገኙ)፡፡

ሌላው የሙእሚኖች ባሕርይ ደግሞ ከቃላትም ሆነ ከተግባር ውድቅ ነገሮችን መራቅ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَالَّذِينَ هُمْ عَنِ اللَّغْوِ مُعْرِضُونَ}**

(እነዚያም እነርሱ ከውድቅ ንግግር ራቂዎች፡፡) ሙእሚኖች ከርካሽ ነገሮች ራሳቸውን የሚያርቁ ሲሆን ለጠቃሚ ነገሮች ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَإِذَا سَمِعُوا اللَّغْوَ أَعْرَضُوا عَنْهُ}**

(ውድቅንም ቃል በሰሙ ጊዜ ከእርሱ ይርቃሉ፡፡) እንድህም ይላል፡

**{وَالَّذِينَ لا يَشْهَدُونَ الزُّورَ وَإِذَا مَرُّوا بِاللَّغْوِ مَرُّوا كِرَامًا}**

(እነዚያም እብለትን የማይመሰክሩ፤ በውድቅ ቃልም (ተናጋሪ አጠገብ) ባለፉ ጊዜ የከበሩ ኾነው የሚያልፉት ናቸው፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡ (የአንድ ሰው እምነት ምሉእነት የሚታወቀው ከማይመለከተው ነገር በመራቁ ነው)፡፡

ሌላው የሙእሚኖች ባሕርይ ምጽዋት መስጠት፣ በመልካም ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል የሚሉትን ያካትታል፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَالَّذِينَ هُمْ لِلزَّكَاةِ فَاعِلُونَ}**

(እነዚያም እነርሱ ዘካን ሰጭዎች፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{وَالْمُؤْمِنُونَ وَالْمُؤْمِنَاتُ بَعْضُهُمْ أَوْلِيَاءُ بَعْضٍ يَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنْكَرِ وَيُقِيمُونَ الصَّلاةَ وَيُؤْتُونَ الزَّكَاةَ وَيُطِيعُونَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ أُولَئِكَ سَيَرْحَمُهُمُ اللَّهُ إِنَّ اللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ}.**

(ምእምንና ምእምናትም ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡፡ በደግ ነገር ያዛሉ፤ ከክፉም ይከለክላሉ፡፡ ሶላትንም ይሰግዳሉ፡፡ ዘካንም

ይሰጣሉ፡፡ አላህንና መልክተኛውንም ይታዘዛሉ፡፡ እነዚያን አላህ በእርግጥ ያዝንላቸዋል፡፡ አላህ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና፡፡)

ሌላው የሙእሚኖች ባህርይ ደግሞ፡ አነሱ ጥብቆችና አላህን ፈሪ መሆናቸው ነው፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَالَّذِينَ هُمْ لِفُرُوجِهِمْ حَافِظُونَ *إِلَّا عَلَى أَزْوَاجِهِمْ أَوْ مَا مَلَكَتْ أَيْمَانُهُمْ فَإِنَّهُمْ غَيْرُ مَلُومِينَ}**

(እነዚያም እነርሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት (አገኙ)፡፡ በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዟቸው (ባሪያዎች) ላይ ሲቀር፡፡ እነርሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሚም እንድህ በማለት ከአላህ ዘንድ ጥብቅነትን ይለምኑ ነበር፡

**(اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الهُدَى وَالتُّقَى والعَفَافَ وَالغِنَى)**

ሙሐመድ ኢብን አልሐነፊያ የተባሉት ሊቅ እንድህ ይሉ ነበር፡ ‹‹የአንድ ሰው ታላቅነት በሦስት ነገሮች ይሟላል፡፡ እነሱም በሃይማኖት ጥብቅነት፣ በመከራ ጊዜ ታጋሽነትና የእለት ከእለት የሕይዎት ሁኔታዎችን ማስተካከል›› የሚሉት ናቸው፡፡

ሌላው የሙእሚኖች ባህርይ አደራን መጠበቅ፤ ቃል ኪዳንን ማክበር የሚሉትን ያካትታል፡፡ እውነተኛ ሙእሚን ገበሬ ለእርሻው እንድሁም የእጅ ባለሞያ ለጥበቡ ትኩረት እንደሚሰጥ ሁሉ ለታማኝነቱ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ እምነትና ቃል ኪዳን የተሳሰሩ መሆናቸውን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡፡

**{وَالَّذِينَ هُمْ لِأَمَانَاتِهِمْ وَعَهْدِهِمْ رَاعُونَ}**

(እነዚያም እነርሱ ለአደራዎቻቸውና ለቃል ኪዳናቸው ጠባቂዎች፡፡) እንድህም እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَوْفُوا بِالْعُقُودِ}

(እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በቃል ኪዳኖች ሙሉ፡፡) እንድህም ይላል፡

{إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُكُمْ أَنْ تُؤَدُّوا الْأَمَانَاتِ إِلَى أَهْلِهَا}

(አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዛችኋል፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ የእምነትና የታማኝነትን ትስስር እንድህ በማለት ገልጸውታል፡ ( ታማኝነት የሌለው ሰው እምነት የለውም፡፡ ቃል ኪዳኑን የማይጠብቅም ሃይማት የለውም)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

አለህ (ዐ.ወ.)ን ዘወትር የሚያወሱና በሱ መመካታቸውን የሚያሳምሩ መሆናቸው ሌላው የሙእሚኖች ባህርይ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُمْ بِذِكْرِ اللهِ أَلَا بِذِكْرِ اللهِ تَطْمَئِنُّ القُلُوبُ}

((እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ፡፡) እንድህም ይላል፡

{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ}

(ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡)

ትክክለኛ በአላህ መመካት ደግሞ አንድ ባሪያ ነገሮችን ሁሉ ለአላህ መተው ነው፡፡ ይህ ተግባር ታድያ ሰበቦችን በማድረስ፣ ጠንክሮ በመስራትና በታታሪነት እንጅ ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( እናንተ በትክክል በአላህ የምትመኩ ቢሆን ኖሮ ማለዳ ሆደ ባዶ ሆኖ ውጥቶ ማታ ሆድን ሞልቶ የሚመለስን ወፍ እንደሚለግስ ሁሉ ሲሳይን በለገሳችሁ ነበር)፡፡

እውነተኛ እምነት ዱካው ወደማህበረሰቡ ሁሉ ይሰፋል፡፡ እውነተኛ ሙእሚን አታላይ፣ ምናፍቅ፣ ውሸታም፣ ቃሉን የሚበላና ከዳተኛ አይሆንም፡፡ የእውነተኛ እምነት አላማ የባለቤቱን መንፈስ ያጸዳል፡፡ እውነተኛ ሙእሚን ዓይነፋር፣ ለጋስና ሰውችን የሚላመድና ሰዎችም የሚለምዱት ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{ثُمَّ كَانَ مِنَ الَّذِينَ آمَنُوا وَتَوَاصَوْا بِالصَّبْرِ وَتَوَاصَوْا بِالْمَرْحَمَةِ}**

(ዐቀበቲቱን አልወጣም)፡፡ ከዚያም ከነዚያ ከአመኑትና በመታገስ አደራ ከተባባሉት፣ በማዘንም አደራ ከተባባሉት ሰዎች አልኾነም፡፡) እንድህም ይላል፡

**{وَالْعَصْرِ * إِنَّ الْإِنسَانَ لَفِي خُسْرٍ * إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَتَوَاصَوْا بِالْحَقِّ وَتَوَاصَوْا بِالصَّبْرِ}**

(በጊዜያቱ እምላለሁ፡፡ ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው፡፡ እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እነድህ ይሉ ነበር፡ (በአላህና በመጨረሻቱ ቀን የሚያመን ሰው ጎረቤት አያስቸግር፡፡ በአላህና በመጨረሻቱ ቀን የሚያመንም እንግዳውን ያክብር፡፡ በአላህን ነመጨረሻቱ ቀን የሚያምን ደገን ነገር ይናገር ወይም ዝም ይበል)፡፡

እኛ በአሁኑ ወቅት ጸጥታ፣ መረጋጋት፣ የመንፈስ ርካታ፣ በዚህችና በምጭውም ዓለም ደስታ እንዲናገኝ በእምነት መርሆች መመራት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{أُولَئِكَ هُمُ الْوَارِثُونَ*الَّذِينَ يَرِثُونَ الْفِرْدَوْسَ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ}**

(እነዚያ ወራሾቹ እነርሱ ናቸው፡፡ እነዚያ ፊርደውስን (ላዕላይ ገነትን)፤ የሚወርሱ ናቸው፡፡ እነርሱ በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡) እንድህም ይላል፡

**{إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ فَلَهُمْ أَجْرٌ غَيْرُ مَمْنُونٍ}**

(ግን እነዚያ ያመኑት መልካሞችንም የሠሩት ለእነርሱ ተቆራጭ ያልኾነ ምንዳ አልላቸው፡፡) አሁንም እንድህ ይላል፡

**{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَانَتْ لَهُمْ جَنَّاتُ الْفِرْدَوْسِ نُزُلًا * خَالِدِينَ فِيهَا لَا يَبْغُونَ عَنْهَا حِوَلًا}.**

(እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው፡፡ በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ከእርሷ መዛወርን የማይፈልጉ ሲኾኑ፤ (መስፈሪያቸው ነው)፡፡

ጌታችን ሆይ እመነትን ለኛ ተወዳጅ አርግልን በልባችንም የተዋበ አደርገው፡፡ አሚን፡፡